ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) {የአላህ እርዳታና (መካን) መክፈት በመጣ ጊዜ፤} [አንነስር:1] የሚለው ምዕራፍ በርሳቸው ላይ ከወረደ በኋላ በሚሰግዱት ሶላት ውስጥ ሁሉ "ሱብሓነከ ረብበና ወቢሐምዲከ አልላሁምመግፊርሊ

ከአማኞች እናት ዓኢሻ - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተላለፈው እንዲህ አለች: «ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) {የአላህ እርዳታና (መካን) መክፈት በመጣ ጊዜ፤} [አንነስር:1] የሚለው ምዕራፍ በርሳቸው ላይ ከወረደ
በኋላ በሚሰግዱት ሶላት ውስጥ ሁሉ "ሱብሓነከ ረብበና ወቢሐምዲከ አልላሁምመግፊርሊ" ይሉ ነበር።» ትርጉሙም "ጌታችን ሆይ!
ከምስጋና ጋር ጥራት የተገባህ ነህ! አላህ ሆይ! ማረኝ።" ማለት ነው። ከእናታችን ዓኢሻ እንደተላለፈው እንዲህም ብላለች: የአላህ መልክተኛ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) ቁርአን ላይ የመጣውን ትእዛዝ ወደ ተግባር ለመለወጥ በሩኩዓቸውና
በሱጁዳቸው ወቅት "ሱብሓነከ ረብበና ወቢሐምዲከ አልላሁምመግፊርሊ" ማለትን ያበዙ ነበር። [ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

የአማኞች እናት ዓኢሻ - አላህ መልካም ሥራዋን ይውደድላትና - እንደተናገረችው ነቢዩ (የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን) {የአላህ እርዳታና (መካን) መክፈት በመጣ ጊዜ፤} የሚለው ምዕራፍ የወረደላቸው ጊዜ ቁርአኑን ወደ ተግባር ለመለወጥ {ጌታህን ከማመስገን ጋር አጥራው! ምህረትንም ለምነው።} የሚለውን የአላህን ትእዛዝ ፈጥነው ለመፈፀም በሶላት መሀል በሩኩዓቸውና በሱጁዳቸው ወቅት እንዲህ ማለትን ያበዙ ነበር፡ "ሱብሓነከ" ለአንተ ከማይመጥን ከሁሉም ጉድለት አንተን አጠራኸለሁ። "አልላሁምመ ረበና ወቢሐምዲክ" ዛትህ፣ ባህሪህና ድርጊትህ ምሉዕ ስለሆነ ምስጉን በሆኑ ውዳሴዎች አወድስሃለሁ። "አልላሁምመግፊርሊ" ከኔ ላይ ወንጀሌን አብስ! ይቅር በለኝ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/5212